ንጽህት ዘአልባ ርስሐት!

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

በመምህር ኅሩይ ኤርምያስ

ግንቦት ፳፻፬ ዐ/ም

በዚህ ትምህርታዊ ጽሑፍ ከጥንተ አብሶ ጋር በተያያዘ አሁን አሁን ጐላ ብሎ መሰማት የጀመረው *"እመቤታችን ጥንተ አብሶ ነበረባት፤ በብስራት ጊዜ ጠፋላት"* የሚል መንፈስቅዱስ ያልገለጠው መጽሐፍ ያልተናገረው ሥርዋጽ ከመሰማትና ከመነበብ አልፎ *'ትክክለኛው ኦርቶዶክሳዊ እምነትና ትምህርት'* የሚል የሃይማኖት ቡሉኮ ተደርቦለት በመለፈፉ አልፎ አልፎ ክርክርና ሙግት ሊያስነሣ መጀመሩን በመግለጽ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ስለጥንተ አብሶ የምታምነውንና የምታስተምረውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት እንድገልጥላቸው በጠየቁኝ ምእመናን ጥያቄ መነሻነት ጊዜና ዕድል ገጥሟቸው የሚያነቡት ምእመናን ሁሉ ስለጥንተ አብሶ ምንነትና እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጥንተ አብሶ ነበረባት ወይስ አልነበረባትም? ስለሚለው ጥያቄ በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው በመንፈስቅዱስ ገላጭነት በመጻሕፍት ዋቢነት ሊቃውንት ካስተማሩት መምህራን ካመሰጠሩት ወስጄ ጥቂት ለማስረዳት እሞክራለሁ።

በቅድሚያ 'ጥንተ አብሶ ምንድር ነው?' የሚለውን እንመልከት

ጥንተ አብሶ ማለት 'የበደል መጀመሪያ' ወይም 'የመጀመሪያ በደል' ማለት ነው፤ የመጀመሪያ በደል ተብሎ የሚጠራውም አዳምና ሔዋን ገና በገነት ሳሉ የፈጸሙት በደል ነው:: ይህስ እንደምን ነው ቢሉ ጌታ አዳምን ፬ቱን ባሕርያተ ሥጋ አስማምቶ ፫ቱን ግብራተ ነፍስ ሰጥቶ በመልኩና በምሳሌው ዐዋቂ ለባዊ አድርጎ ፈጠረው ፤ ከጎኑም አንዲት አጥንት ወስዶ ሔዋንን ፈጠረ። ፈጥሮም እንዲሁ አልተዋቸውም በልጅነት አክብሮ በመግዛት አሠልጥኖ በገነት አኖራቸው። እነርሱም ፯ቱን ዓመታት በተፈጠሩበት ግብር ጸንተው ትእዛዙን አክብረው በገነት ኖሩ። ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ በልሳነ ከይሲ ተሠውሮ በአሳች ምክሩ አሳታቸው፣ "**አትብሉ**" ከተባሉት ከዕፀ በለስ ቅጠል ቀጠፉ፡ አምላክ መሆንንም ሽተው የቀጠፉትን ቅጠል በሉ፤ በዚህ ጌታቸውን አሳዘኑት ትእዛዙን ሽረው በደሉት። ጌታም ኰናኒ በርትዕ ፈታሒ በጽድቅ ነውና **"ከእርሱ በበላችሁ ጊዜ ሞትን ትሞታላችሁ"** ብሎ ቢበድሉ የሚያገኛቸውን መከራ አስቀድሞ እንደነገራቸው በሞተ ሥጋ ሞተ ነፍስን በርደተ መቃብር ርደተ ገሃነምን ፈረደባቸው **"ወፈትሖሙ በአዳም ወበሔዋን በሞት ለዝሉፉ = በአዳምና በሔዋን ለዘላለም ምትን ፈረደባቸው"** እንዲል።

ጥንተ አብሶ የሚባለው ሰውን ሁሉ ያስጎዳው ይህ የመጀመሪያውና ታላቁ በደል ሲሆን ሊቃውንት በየአባባላቸው ጠርተውታል ቅ/ አትናቴዎስ "ጥንተ አብሶ" "ኃጢአተ አዳም"፣ ቅ/ ቄርሎስ "ጥንተ ኃጢአት" ሳዊሮስና ቅ/ ኤፍሬም "ዘቀዳሚ መርገም" ብለውታል። ይህም የውርስ ኃጢአት ሆኖ ከወላጅ ወደ ልጅ እየተላለፈ ሰውን ሁሉ የሚገዛ ሆነ። ሐዋርያው ጳውሎስ **"ቀነዮሙ ሞት እምአዳም እስከ ሙሴ = ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛቸው"** እንዳለ አዳምና ሔዋን ብቻ ያይደሉ ከእነርሱ የተወለዱ ልጆችና የልጅ ልጆቻቸው ሁሉ በደለኞች ሆኑ ፡ ባሕርየ ሰብእ ጐሰቈለ፡ ንጽሐ ጠባይዕ አደፈ፡ ኃጢአት በሰው ልጆች ደጅ አደባች ብዙዎችንም አጠመደች፡ ስለዚህም ተላልፈው ለሞትና ለሲኦል ተሰጡ። ቅዱሳን እነአብርሃም ነቢያት እነሳሙኤል እንኳ ቢሆኑ ንጽሐ ጠባይዕ ስላደፈባቸው በግዝረታቸው በመሥዋዕታቸው ራሳቸው መዳን ሌላውንም ማዳን ተሳናቸው ሁሉም ወደሲኦል ወረዱ፤ በሲኦልም ኃጥአንን መከራ ነፍስ ጸናባቸው ጻድቃንን ግን ረድኤተ እግዚአብሔር ጠበቀቻቸው ፤ ሃይማኖት ትሩፋታቸው ግን ወደሲኦል መውረድን አላስቀረላቸውም:: ዘፍ፩፥፳፯ ፥ ፫፥፩-፲፬ ሮሜ፭፥፲፬ ሃ/አበ ፸፥፲፱ ፣ ፹፯፥፯ ፥ ፻፬፥፰ ውዳ.ዘኅ

በማኅፀን የሚቆራኝ ፈቃደ ልቡናንም ወደ ገቢረ ኃጢአት የሚያዘነብል ይህን የውርስ ኃጢአት በኃጢትም ምክንያት በባሕርየ ሰብእ ጸንቶ የነበረውን ፍዳ መርገም ሊያጠፋ ከሦስቱ አካላት አንዱ ወልድ ሰው በሚጸነስበት ልክና ሥርዓት በድንግል ማርያም ማኅፀን ተፀነሰ፡ ሰው ሆኖም ተወለደ። **"ተፀንሰ ወተወልደ በሥጋ ያሰስል ትካዘ ዘልደተ ደቂቅ ወያግዕዝ ትዝምደ ዕጓለእመሕያው = ሕፃናት በተወለዱ ጊዜ የሚጣባቸውን ቁራኝነት ያርቅ ዘንድ የሰውንም ባሕርይ ከቀደመ ፍዳ ያድን ዘንድ ተፀነሰ ተወለደ"** ሳዊሮስ ሃ/አበ ፹፯፥፯

ነገርግን ለመወለዱ ዘርዕ ምክንያት አልሆነውም፡ ሥጋዊም አባት አላሻውም፡ በንጽሕና በቅድስና ጸንታ ከኖረች ከድንግል ያለአባት ተፀነሰ፤ ሕማም ድካም ሳያገኛት በሴቶች የሚደርሰውም ሳይደርስባት ተወለደ እንጂ። ፍጹም ጌታ ፍጽምት በሆነች በእመቤታችን ማኅፀን አደረ፣ ቡሩክ አምላክ "ቡርክት አንቲ" ተብላ በመልአኩ ቃል በኤልሳቤጥም ቃል ከተመሰገነች ከድንግል ተወለደ፤ ቡርክት ማኅፀን የቡሩክ አምላክ ማደሪያ ሆነች፡ ቅድስት ማኅፀን ቅዱስ ጌታን በሥጋ አስገኘች፤ ከመርገም በፊት ከነበረች ቡርክት ምድር አዳም ያለእናት ያለአባት ተፈጠረ፡ ዳግማይ አዳም ክርስቶስም

ኃጢአተ አዳም ከሌለባት መርገመ ጌባል ካልወደቀባት ቡርክት ማርያም ተወለደ፤ ከድንግል የተወለደ ጌታ ነውር ነቀፋ የሌለበት ንጹህ እንደሆነ የወለደችው ድንግልም ነውር ነቀፋ የሌለባት ንጽህት ናት፤ እርሱ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ቅዱስ እንደሆነ እርሷም በጊዜ ሁሉ ቅድስት ናት፡-

- **“ንጽህት ኩሎ ጊዜ ንስእል ወናንቀዐዱ ጎቤኪ = ሁልጊዜ ንጽህት የምትሆኚ ሆይ ዓይነ ልቡናችንን ወዳንቺ እንሰቅላለን”** ቅ/ኤፍሬም ውዳ.ዘሰ

- “**እስመ ፍጹም ውእቱ በላዕሉ ወፍጹም በታሕቱ ለምንትኑ ጎደረ ፍጹም ውስተ ፍጹም = እርሱ በላይ ፍጹም ነው በታችም ፍጹም ነው ስለምን <u>ፍጹም በፍጹም</u> አደረ ይባላልን”** እንዳለ ኤጲፋንዮስ። ሃ/አበ ፶፮፥ ፴፯

በባሕርየ መለኮቱ ጽድቅ እንጂ ኃጢአት ሕያውነት እንጂ መዋቲነት የማይስማማው አምላክ የቸርነት ሥራውን ለመሥራት እናት ትሆነው ዘንድ ከሴቶች መካከል መርጦ ትህትናን እንደ ዝናር አስታጥቆ ንጽህናን እንደ አክሊል አቀዳጅቶ ካዘጋጃት ከቅድስት እናቱ በኃጢአት ምክንያት ለሞት የተሰጠ ሥጋን ነሣ፡ የነሣውንም ሥጋ በተዋህዶ ከባሕርየ መለኮቱ ጋር አንድ አደረገው። ሥጋን ተዋህዶ ስለተወለደ ግን በባሕርየ ሰብእ ፀንቶ የነበረ መርገመ ሥጋ አላገኘውም፤ ድንግልም ከደቂቀ አዳም ወገን ስለሆነች በጌታ ዘንድ ሞገስን ያገኙ ደጋጎች ቢሆኑም ንጽህ ጠባይዕ ያደፈባቸው ልጆችን እንደወለዱ እንደ ሳራ እንደ ርብቃ ገና በማኅፀን ሳለ መርገም የሚጣባው ኃጢአተ አበው የሚቆራኘው ዕሩቅ ብእሲ የወለደች አይደለችም፡ የዚህ ዓለም ርኩሰት እንዳያገኛት ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስቅዱስ የጠበቃት ንጽህት እንደመሆኗ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሳለው ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ተብሎ የሚመሰገን የቅድስናው መጠን የንጽህናው ልክ የማይሰፈር የማይለካ ፍጹም ጌታን ወለደች እንጂ።

- **“ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ = ከአንቺ የሚወለደውም ቅዱስ ነው”** ሉቃ ፩፥፴፭

- **“ዘአልቦቱ ጥንት ተወክፈ ሎቱ ለባሕቲቱ ህላዌ ሥጋ ዘቦቱ ጥንት ዘነሥአ እምእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም <u>ንጽህት ዘእንበለ ርስሐት</u> = መጀመሪያ የሌለው እርሱ <u>አደፍ ጉድፍ የሌለባት ንጽህት</u> ከሆነች ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም የነሣውን መገኛ ያለውን የሥጋ ባሕርይ ተዋህደ”** ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ ሃ/አበ ፴፭፥፲፪
- **“ወጎደረ ውስተ ከርሠ ድንግል ማርያም <u>ንጽህት ዘአልባቲ ርስሐት</u> ወላዲተ እግዚአብሔር = አምላክን የወለደች <u>አደፍ ጉድፍ የሌለባት ንጽህት</u> በሆነች በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ”** ዲዮናስዮስ ሃ/አበ ፶፩፥፲፬

- “ለብሰ ሥጋ ዘኃጢአት እምወለቶሙ ለኃጥአን እንተ ይእቲ <u>ንጽህት በሥጋሃ ወቅድስት በነፍሳ ወኢለከፌ ኃጣውአ አበዊሃ ለወልዳ</u> = <u>በሥጋዋ ንጽህት በነፍሷም ቅድስት</u> የሆነች፡ ኃጢያተ አዳም የነበረባቸው ሴት ልጅ ፤ ከእርሷ በኃጢአት የጐሰቆለ ሥጋን ለበሰ ነገር ግን <u>የአባቶቿ ኃጢአት አላገኘውም</u>” አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መጽ/ምሥ ፲፱፥፶፩

ከድንግል የተወለደ ክርስቶስ ኢየሱስ በሰው የተፈረደውን መከራ ተቀብሎ ሰውን ለማዳን ሰው ቢሆንም ቅሉ ዕድፈት ርኩሰት ያላገኘው ንጹህ ቅዱስ እንደሆነ አምላክን የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምም እድፈት ርኩሰት የሌለባት ንጽህት ቅድስት መሆኗን ከተረዳን እንግዲህ መቼና እንዴት እንደነጻች እንመለከታለን።

ጥንተ አብሶ የለባትም አልነበረባትም ማለትን ስህተት ጥንተ አብሶ ነበረባት ማለትን ደግሞ ትክክለኛ አርቶዶክሳዊ ትምህርት አድርጎ ለማሳየት የሚሞክሩቱ ንጽህት ናት የነጻችው ግን ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ጌታ ከእርሷ የመወለዱን የምስራች ባበሰራት ጊዜ መንፈስቅዱስ አነጻት ቀደሳት ይላሉ ፤ ለዚህም ከሐዋርያት ቅዱስ ጳውሎስ “**ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ የበደሉትንም ያልበደሉትንም ሞት ገዛቸው**” (ሮሜ፭፥፲፬) ፤ ከሊቃውንትም ቅዱስ ያሬድ **“አንዲሆ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ ጎደረ ላዕሌሃ = ሥጋዋን አነጻ እርሷን ቀደሰ በርሷም አደረ”** (ዚቅ ዘአስተርእዮ) ያሉትን እንደ ማስረጃ ሲጠቅሱ በተጥባበ ነገር ለኦርቶዶክሳዊ ትምህርት ለኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያንም መቅናት የሚመስል ያልጠራ ቀናዒነትን ፈጥሮ የቀናውን ኦርቶዶክሳዊ ትምህርት ለማስጣል *“ጥንተ አብሶ የለባትም ማለት ሰው/ሴት አይደለችም ማለት ነው ይህም የካቶሊክ እንጂ የኦርቶዶክስ እምነት አይደለም፣ ጥንተ አብሶ የለባትም ማለት የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ከኢኃት አብያተ ክርስቲያናት እንዳይለያት ያሰጋል”* ሲሉ ይደመጣል።

እዚህ ላይ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ስታስተምር የኖረችው አሁንም የምታስተምረው ከጠራ ምንጭ ከትምህርተ ሐዋርያት የተቀዳውንና ከጥንት ከመሠረቱ በመንፈስቅዱስ ተከነዋውኖ የተሰጣትን እምነትና ትምህርት ብቻ

እንጂ ተቋማትን ወይም ሰዎችን ለማስደሰት ለመመሳሰል ለወዳጅነት ለአንድነት ተብሎ የሚቀነስ የሚጨመር የሚቸረቸር የሚመነዘር ትምህርት እንደሌላት ሊኖራትም እንደማይችል መገንዘብ ይገባል፤ ከመጻሕፍት ያገኘነውን እርሱን እንናገራለን ከሊቃውንት የተማርነውን እርሱን እንመሰክራለን።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሴት መሆኗን አንጠራጠርም፤ ስንኳን ስትነቀፍ ውዳሴዋም ሲነገር ሲተረጐም ብንሰማ በልብ ሰሌዳ የታተመ ፍጹም ፍቅር የሚያፈልቀው ፅንባን በማንባት ካልሆነ በቀር በመጻፍም ቢሆን በመናገርም ቢሆን ፍቅራችንን መግለጥ እስኪያቅተን ድረስ ከምንም በላይ አልቀን ብንወዳትም ከሰማይ ወረደች አንልም፤ መጻሕፍት እንደነገሩን አበው እንዳስተማሩን ከዳዊት ከሰሎሞን ወገን ኢያቄም እና ሐና ከተባሉ ቡሩካን ወላጆች የተወለደች በሰው ሁሉ አካል ያሉት ሥጋ ነፍስና መንፈስ ያሏት የአዳምና የሔዋን ልጅ መሆኗን እናምናለን። ሙቀት ልምላሜ ከተለያቸው አረጋውያን ወላጆች በመልአክ ብስራት በመወለድ የመወለጃ ክብር እጅግ ከፍ ከፍ አለ፤ ዘጠኝ ወር በማኅፀን በመቆየትና በግዕዘ ሕፃናት በመወለድ ግን ከሴቶች ሁሉ የተለየች አይደለችም። በማኅፀን ሳለች የእናቷ ጥላ ያረፈበት ሙት ተነሥቶ እጅ መንሣቱ የእናቷን ማኅፀን የዳሰሰች ዕውር ዐይን መብራቱ የመወለጃን ክብር ልዩ አደረገው፤ ሦስት ዓመት እስኪሆናት ድረስ ጡት ጠብታ በሜዳ ድሃ በማደግ ግን ከሴቶች አልተለየችም። ምድራዊ ያይደለ በሰማያዊ መልአክ እጅ እየመጣላት ሰማያዊ ምግብ እየተመገበች ሰማያዊ መጠጥ እየጠጣች ፲፪ ዓመት በቤተመቅደስ በመኖሯ ከሴቶች መካከል የተመረጠች መሆኗ ተገለጠ፤ ግምጃ ፈትላ ሰፍታ ማይ ቀድታ ቤተመቅደስ በማገልገል ደቂቀ ዮሴፍን ዘመድ ዘመድ በማለት ግን ከሴቶች አልተለየችም። ልማደ አንስት ዘርዐ ወራዙት ሳይኖርባት ጌታን ያለ አባት በመፅነሷ ከሴቶች ተለየች፤ ፱ ወር ከ፭ በመፅነስ ግን ከሴቶች አልተለየችም። ሕማም ሳያገኛት ድንግልናዋ ሳይለወጥ ፈጣሪዋን በመውለዷ ከሴቶች ሁሉ ከፍጥረታትም ሁሉ ይልቅ የከበረች ሆነች ፤ ጡት በማጥባት በጀርባዋ አዝላ በደረቷ አቅፋ በማሳደግ ግን ከሴቶች አልተለየችም። እንደልጇ ከሙታን ተነሥታ በማረጓ በልጇም ቀኝ በመቀመጧ ከሰው ሁሉ በክብር በጸጋ ትለያለች ከፍ ከፍ ትላለች ፤ ሞትን በመቅመስ በመገነዝና በመቀበር ግን ከሰው ሁሉ አልተለየችም።

- **“ወሶበ ተፍህረት እሙ ማርያም ለዮሴፍ ዘእንበለ ይትራከቡ ተረክበት ፅንስተ እመንፈስቅዱስ = እናቱ ማርያምም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስቅዱስ ፀንሳ ተገኘች”** ማቴ ፩፥፲፰

- **“አ ድንግል አኮ በፍትወተ ደነስ ዘተፀነስኪ አላ በሩካቤ ዘበሕግ እምሐና ወኢያቄም ተወለድኪ = ድንግል ሆይ በኃጢአት ፍትወት የተፀነሽ አይደለሽም በሕግ በሆነ ሩካቤ ከሐናና ከኢያቄም ተወለድሽ እንጂ”** አባ ሕርያቆስ ቅ/ማር ቁ ፴፰

- **“እስመ ነሥአ ሥጋ መዋቴ እስመ ቅድስት ድንግል ማርያም እንተ ነሥአ እምኔሃ መዋቲት ይእቲ = ሟች ሥጋን ተዋሀደ ሥጋን ከእርሷ የነሣ ቅድስት ድንግል ማርያም ሟች ናትና”** ቅ/ አትናቴዎስ ሃ/አበ ፳፫፥፲፩

- **“ወጎደረ ውስተ ከርሳ ለእንተ ተወልደት እምአብ ወእም እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም = ከአባትና ከእናት በተወለደች በእመቤታችን ማኅፀን አደረ”** ጎርጎርዮስ ነባቤ መለኮት ሃ/አበ ፷፥፲፭

- **“እንተ ይእቲ ማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ እምነ ሥርዉ ለአዳም እንተ ሠረፀት ለነ = ይህቺውም ከአዳም ሥር የበቀለችልን አምላክን የወለደች እመቤታችንና የድኅነታችን ምክንያት ማርያም ናት”** ቅዱስ ያሬድ ዚቅ ዘጥር እንጦንስ

ከሰው ወገን የተገኘች ሴት ናት ማለት ግን የውርስ ኃጢአት አግኝቷታል ንጽሐ ጠባይዕ አድፎባታል ማለት አይደለም፤ ጌታ ለሰው ልጆች ሊያደርግ ላለው የቸርነት ሥራው አስቀድሞ መርጧታልና ሕይወትን የሚያድል የጌታ እናቱ ሞትን ያመጣ ፍዳ መርገም እንዳያገኛት በመርገምም ምክንያት በሥጋ ላይ የተፈረደው ፍርድ እንዳይደርስባት መንፈስቅዱስ ገና በእናቷ ማኅፀን ከርስሐት ከመርገም ጠበቃት ፤ መርገም የሌለበት ጌታን ለመውለድ መርገም የሌለባት ንጽህት ዘር አድርጎ አኖራት፤ ሥጋዋን በኃጢአት ባለመለወጥ ልቡናዋን የሥጋን ነገር ከመሻት በመጠበቅ በንጽህ ሥጋ በንጽህ ነፍስ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ አጸናት። ስለዚህም የአምላክ እናት ድንግል መቼም መች ኃጢአት መርገም ያላገኛ ዐደፍ ጉድፍ የሌለባት መንፈስቅዱስ ከፅንስ እስከ ልደት ከልደት እስከ ዕረፍት ለዘለዓለም ንጽህት ቅድስት ጽሪት ናት፤

ማስረጃ :-

- **“<u>ቀደሰ ማኅደሮ ልዑል = ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ</u>”** መዝ ፵፮፥፬

- **“ኩለንታኪ ሠናይት እንተ ኀቤየ አልብኪ ነውር ወኢምንትኒ ላዕሌኪ = ሁለንተናሽ ውብ ነው በላይሽም ምንም ነውር የለብሽም”** መኃ ፬፥፯

- **“መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ትሔውጽ ከመ ጎህ ጽዕዱት ወብርህት = እንደ ጎህ የምትጐበኝ ንጽህትና የምታበራ ይህች ማን ናት?”** መኃ ፮፥፩

- **“እግዚአብሔር ጸባዖት እመ ኢያትረፈ ለነ ዘርዐ ከመ ሰዶም እምኮነ ወከመ ገሞራ እመሰልነ = አቸናፊ እግዚአብሔር ዘርን ባያስቀርልን ኖሮ እንደ ሰዶም በሆንን ነሞራንም በመሰልን ነበር”** ኢሳ ፩፥፱

- **“ተፈሥሒ ኦ ምልዕተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ፡ ቡርክት አንቲ እምአንስት = ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ”** ሉቃ ፩፥፳፰

- **“መንፈስቅዱስ ዐቀባ እምከርሰ እማ = ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስቅዱስ ጠበቃት”** ሳዊሮስ ሃ/ አበ

- **“ኢያእመረ እስመ ዘተፈጥረት እምነ ጽቡር ጽዩይ ትከውን መቅደሰ ለእግዚአብሔር = ከንጹህ ዘር የተፈጠረች ድንግል የእግዚአብሔር ማደሪያ እንደምትሆን አላወቀም”** ኤራቅሊስ ሃ/አበ ፵፰፥፴፩

- **“ወሰመያ ለእግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲቶ ወፂአ እምከርሳ እንዘ ድንግል ይእቲ ወኢረኩሰት በምንትኒ እምዘፈጠራ = በድንግልና ሳለች ከማኅፀኗ ተወልዶ እመቤታችን ድንግል ማርያምን እናቱ አደረጋት፤ ከፈጠራትም ጀምሮ በምንም ምን አልረከሰችም”** ቴዎዶጦስ ሃ/አበ ፶፫፥፳፪

- **“ወሶበ ረከበ ሥጋሃ ቅዱሰ ላዛቲ ድንግል ወነፍሳ ቅድስተ ፈጠረ ሎቱ መቅደሰ ዘቦቱ ነፍስ = የዚህችን ድንግል ሥጋዋን ቅዱስ ነፍሷንም ቅድስት ሆኖ ባገኘ ጊዜ ነባቢት ነፍስ ያለውን መቅደስ ፈጠረለት”** ዮሐንስ አፈወርቅ ሃ/ አበ ፳፯፥፲፭

- **“ወሶበ ርእየ ንጽሕናኪ ለሊሁ እግዚአብሔር አብ ፈነወ ኀቤኪ መልአኩ ብርሃናዌ ዘስሙ ገብርኤል = ንጽህናሽንም ባየ ጊዜ እርሱ እግዚአብሔር ገብርኤል የሚባል ብርሃናዊ መልአኩን ወዳንቺ ላከ”** አባ ሕርያቆስ ቅ/ማር ቁ ፵፭

- **“ወበከመ ነፋህኩ ውስተ ገጹ ለአዳም ከማሁ አንቲኒ ሀሎኪ ወኢረሳሕኪ = በአዳም ፊት እፍ እንዳልሁበት አንቺም እንዲሁ አለሽ መለወጥም አላገኘሽም”** ሊቃ.ትር

- **“ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሱ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ = ማርያምስ ከጥንት ጀምራ እንደ ጠራ ዕንቁ በአዳም አካል ታበራለች”** ቅዱስ ያሬድ ዚቅ ዘጎዳር ማርያም

- **“ንዒ ርግብየ ኩለንታኪ ሠናይት ፀምር ፀዓዳ እንተ አልባቲ ርስሐት = ሁለንተናሽ ያማረ ርግቤ ሆይ ነዪ፤ አደፍ ጉድፍ የሌለብሽ ንጹህ ግምጃ ሆይ ነዪ”** ቅዱስ ያሬድ ዚቅ ዘጎዳር ቁስቋም

- **“አ ንጽህት ድንግል እፎ ኮነት ለኪ ዕለተ ንጽህ ዛቲ ዕለት ማዕዜኑ ረኰሰኪ ከመ ትኅሢሥያ ለዕለተ ንጽህ እስመ እንበለ ሩካቤ ፀነስኪዮ ወዘእንበለ ርስሐት ወለድኪዮ ኢረኩሰ ሐሪስኪ ለምንትኬ አጌሠኪዮ ለፍሬ ስብሐት ውስተ ቤተመቅደስ አመ ዕለተ ንጽህ እምቤተመቅደስ ትትቄደሲ አንቲ ወእምጽላተ ሰማይኒ ዘውስተ ከርሰ ታቦት ይከብር ወልድኪ = ንጽህት ድንግል ሆይ ይህች ዕለት እንደምን የመንጻት ቀን ሆነችልሽ የመንጻትን ቀን ትሺያት ዘን ድ መቼ ረከሽ? ያለሩካቤ ፀንሰሽዋልና አደፍ ጉድፍ ሳያገኝሽም ወልደሽዋልና መውለድሽም ርኩሰት አላገኘውም። ፍሬ ስብሐት የተባለ ጌታን ስለምን በመንጻት ቀን ወደ ቤተመቅደስ ወሰድሽው ከቤተመቅደስ ይልቅ አንቺ ቅድስት ነሽና በታቦቱም ላይ ካለ የሰማይ ጽላት ይልቅ ልጅሽ የከበረ ነውና!”** አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ መጽ/ምሥ ፱፥፮

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መቼም መች ፍዳ ኃጢአት መርገም ያላገኛት በንጽህና ፍጽምት መሆኗን መጻሕፍት አበሰሩ ፤ የቀደሙ ነቢያት ኋላ የተነሡ ሊቃውንትም ንጽህናዋ ከዚህ እስከዚህ ተብሎ በጊዜ የሚከፈል ሳይሆን ከጥንት እስከ ፍጻሜ ከጽንሰት እስከ ዕርገት ለዘለዓለም መሆኑን ተካክለው መሰከሩ፤ ስለዚህም ጌታን ከመውለዷ አስቀድሞ በወለደችውም ጊዜ ከወለደችውም በኋላ ነውር ኃጢአት የሌለባት መርገም ያላረፈባት በጊዜው ሁሉ ፍጽምት ንጽህት ቅድስት መሆኗን የምትመሰክር አርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያናችን ትምህርቷ ከመጻሕፍት የተቀዳ ከነቢያት ትንቢት ከሊቃውንት ትምህርት ፍጹም የተስማማ መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

“በብሰራት ጊዜ ነዳች” ማለት እስከ ብስራት ድረስ ንጽህት አልነበረችም መርገም ነበረባት ማለት ነው፡ የነቢያትን ትንቢት የሊቃውንትም ትምህርት የመጻሕፍትንም ምስክርነት ማሳበል ነው። እንግዲህ ዳዊት ወደፊት እንደሚደረግ አድርጎ “ልዑል ማደሪያውን ይቀድሳል” ብሎ ያይደለ **“ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ”** አስቀድሞ እንደተደረገ አድርጎ ትንቢት መናገሩ ፤ መልአኩም ወደፊት እንደሚደረግላት ሳይሆን አስቀድሞ እንተደረገላት አድርጎ **“ጸጋን የተመላሽ ሆይ ፤**

ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ” ማለቱ ስህተት ነው ይባላልን? ስህተቱ ይህን ስህተት ለማለት መሞከር ነው! እንደ መጻሕፍቱ ምስክርነት ድንግል ከብስራትም በፊት ንጽሕት መሆኗን ተመልክተናል። በመልአኩ መምጣትና የምስራች ድምፅ የማሰማቱ ታሪክ የሚያስረዳው ድንግል ከዚያ በፊት ንጽህት እንዳልነበረችና በዚያ ቅጽበት መንጻቷን ሳይሆን ከዚያ አስቀድሞ ከጥንት ከመሠረት ንጽህት ሆና መኖሯ ነው፡ ለዚህ ከላይ የጠቀስኩት ማስረጃ በቂ ቢሆንም ከመልአኩ ንግግር “**ቡርክት**” የሚለውን ቃል በተጨማሪነት እጠቅሳለሁ። **“ቡርክት”** ማለት በረከት ያላት፡ያደረባት፡ የተባረከች ፡ የተለየች ፡ የተመሰገነች ማለት ነው ቃል በቃል ሲተረጐም፤ መልአኩ **“ቡርክት አንቲ እምአንስት”** ብሎ በታላፊ ጊዜ ግሥ እንጂ “ትከውኒ ቡርክተ = የተባረከሽ ትሆኛለሽ” ብሎ በመጻኢ ግሥ እንዳልተናገራት እናስተውል። ይህ እንግዲህ በእውነት እመቤታችን አስቀድሞም መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት ንጽህት መሆኗን በግልጥ ያሳያል፤ መልአኩ “ቡርክቲ አንቲ” እያላት *መርገም ነበረባት* ማለት ይህ የመልአኩን ንግግር ግዴፍ ምኑን ማድረግ ነው ምክንያቱም በረከት ካለ መርገም ቅድስናም ካለ ርኩሰት የለምና ልምላሜ ባለበት ይብሰት ብርሃን ባለበት ጨለማ አለ ማለት እንደማይቻል። በዚያውም ላይ የመልአክ ድምፅ ሰምታ ከመርገም ነጻች ማለት ይህ የቀና ሃይማኖት አይደለም። ይህማ ቢሆን ከእመቤታችን በፊት ሎጥ፣ ሙሴ፣ ኢያሱ፣ ዘካርያስ ከመላእክት ጋር ተነጋግረው አልነበረምን? በመልአክ ብስራትስ ሶምሶን ዮሐንስ ተወልደው የለምን? እንግዲህ እነዚህ ሁሉ የመልአክ ድምጽ ስለሰሙ ከመርገም ነጹ ይባላልን? ይህ ስህተት ነው ፍጡር የሚቀደሰው በመንፈስቅዱስ እንጂ በመልአክ ድምጽ አይደለምና። ለሌሎች ያልተደረገ ለእመቤታችን ተደረገላት ፡ ንጉሥ የሚያርፍበትን አዳራሽ የሚያድርበትን እልፍኝ አስቀድመው ጠርገው ወልውለው ምንጣፍ አንጥፈው መጋረጃ ጋርደው ምንጣፍ አንጽፈው ጉዝጓዝ ጐዝጉዘው እንዲያዘጋጁት ለሰማያዊ ንጉሥ ለኢየሱስ ክርስቶስ ማረፊያ ማደሪያ ትሆን ዘንድ ተመርጣለችና መንፈስቅዱስ ገና በማኅፀን ሳለች አነጻት ቀደሳት ኃጢአት ርኩሰት እንዳያገኛት ንጽህ ጠባይዕ እንዳያድፍባት ጠበቃት ፤ በየጊዜውም በጸጋ ላይ ጸጋ በክብር ላይ ክብር እየተጨመረላት ኖረች። መልአኩም የጌታን መወለድ ሲያበስራት **“ምልዕተ ጸጋ”** ፤ **“ቡርክት አንቲ እምአንስት”** ብሎ መንፈስቅዱስ ባለመለወጥ አጽንቶ የጠበቃት ንጽህት ስለመሆኗ እንደሚባርክ በዕበይ ሳይሆን እንደባለሟል በፍጹም አክብሮት ውዳሴ የተሞላ ሰላምታ አቀረበላት ፤ “**መንፈስቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ**” ብሎ የመንፈስቅዱስን ወደርሷ መምጣት ነገራት ፤ ያነጻሻል ይባርክሻል ግን አላላትም አስቀድሞ በንጽህና አጽንቶ ጠብቋታልና ፤ **“ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ”** ብሏት ነበርና በርሷ ማኅፀን የሚፈጸመው የአምላክ ሰው የሰው አምላክ የመሆን ድንቅ ምሥጢር የሚፈጸም በመንፈስቅዱስ ኃይል ጥበብና አዋህጅነት መሆኑን ለማስረዳት **“መንፈስቅዱስ ወዳንቺ ይመጣል”** አላት። ፈቃዱም የሦስቱ ሁሉ እንደሆነ ለማጠየቅ **“ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ”** ብሎ የአብን ለአጽንዖ ፤ “**ዘኒ ይትወለድ እምኔኪ ቅዱስ ውእቱ**” ብሎ የወልድ ሥጋን ለመዋሀድ ወደርሷ የመምጣታቸውንም ነገር ነገራት።

“አንጺሆ ሥጋሃ ቀዲሶ ኪያሃ” የሚለውም የቅዱስ ያሬድ ድርሰት በዚህ ጊዜ ብሎ የጠቀሰው አይደለምና እስካሁን ያልነውን ለሚቃረን ትምህርት ማስረጃ ሆኖ ሊጠቀስ አይችልም ፤ *“ጥንተ አብሶ ነበረባት በብስራት ጊዜ ጠፋላት”* ማለትን እንጂ ያነጻት የቀደሳትና ያከበራት ጌታ እግዚአብሔር መሆኑን እናምናለን እንመሰክራለንና ፤ ይህም ገና በማኅጸን የተፈጸመላትን በንጽህና በቅድስና የጠበቃት መሆኑን መናገር እንጂ ሌላ አለመሆኑን ከፍ ብዬ የጠቀስኩት “**“ማርያምሰ ተሐቱ እምትካት ውስተ ከርሱ ለአዳም ከመ ባሕርይ ፀዓዳ = ማርያምስ ከጥንት ጀምራ እንደ ጠራ ዕንቍ በአዳም አካል ታበራለች”** ባለው ምስጋናው ይታወቃል።

ስለዚህም በመጻሕፍት ምንጭነት አርቶዶክሳውያን ሊቃውንት እንዳስተማሩን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኃጢአተ አዳም የሌለባት መርገም ያልደረሰባት መቼም መች ንጽህት ሆና እንድትገኝ መንፈስቅዱስ ከአባት ዘር ከእናት ደም ተከፍሎ በሐና ማኅፀን ከተፀነሰችበት ቅጽበት አንሥቶ የጠበቃት ንጽህተ ንጹህን ቅድስተ ቅዱሳን ናት ብለን እናምናለን እንመሰክራለን ፤ ጥንተ አብሶ የለባትም ስንልም ከሰው ወገን አይደለችም እያልን አይደለንም ከሰው ወገን የተመረጠች የባሕርያችን መመኪያ ናት እንላለን ፤ *“ይልቁንም ከሰው ወገን ሊይደለችም”* የሚሉትን ሊቁ በኂኛ ግዘት **“እመቦ ዘይብል ከመ ድንግል ቅድስት ይእቲ ኃይል አርያማዊት ውጉዘ ለይኩን = ቅድስት ድንግል ከሰማይ የወረደች ኃይል ናት የሚል ቢኖር የተለየ ይሁን”** ሃ/አበ ፱፳፫፥ ፷ እንዳለ ሊሉያን ፍሉጣን ናቸው እንላለን። በድፍረት *“ሴት ናት መርገም ነበረባት”* የሚሉትንም ሊቁ ኢትዮጵያዊው ቅዱስ “**ወኢይበጽሖሙ ጽላሎተ መንፈስቅዱስ ለዘአርኩሱ ዜናሃ = የድንግልን ዜና ያረካከሱትን የመንፈስቅዱስ ጥላ አይጋርዳቸውም**” መጽ/ምሥ ፲፩፥፯ እንዳሉ ከበረከተ መንፈስቅዱስ ውጪአን መሆናቸውን እንመሰክራለን።

ስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
አሜን።